የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No 22
ADDIS ABABA 14th January, 2015

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፴፪/፳፻፯ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝናኦዲት ቦርድን ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ገጽ ፯ሺ፱፻፶፰

## CONTENTS

Regulation No. 332/2014

Establishment and Determination of the Procedure of the Accounting and Auditing Board of Ethiopia Council of Ministers Regulation …………….Page7958

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፪ /፳፻፯

## የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን ለማቋቋም እና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፩ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፳፻፭ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና ፴፭ እና በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፳፻፮ አንቀጽ ፬(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፪/፳፻፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.332 /2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT AND TO DETERMINE THE PROCEDURE OF THE ACCOUNTING AND AUDITING BOARD OF ETHIOPIA

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013) and Article 4(1) of the Financial Reporting Proclamation No. 847/2014.

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Establishment and Determination of the Procedure of the Accounting and Auditing Board of Ethiopia Council of Ministers Regulation No. 332/2014".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 20.95

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ "አዋጅ" ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ ነው፤

፪/ "ድርጅት" ማለት የሂሣብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ በቦርዱ የተመዘገበ ድርጅት ነው፤

፫/ "ባለሙያ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት እንደተመ ሠከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሠከረለት ኦዲተር በቦርዱ የተመዘገበ እና እንደ አግባብነቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

### ፬.ዋና መሥሪያ ቤት

የቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

### ፭. የቦርዱ ዓላማዎች

ቦርዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ በሪፖርት አቅራቢ አካላት የሚቀርቡ የፋይናንስ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሪፖርቶች አዘገጃጀት እና አቀራረብ ጥራት ማስጠበቅ፤

፪/ የኦዲተሮች እና የሂሳብ ባለሙያዎችን የሙያ ደረጃ ማስጠበቅ፤

፫/ የሂሳብ አያያዝና የኦዲት አገልግሎትን ጥራት ማስጠበቅ ፤

፬/ የሂሣብ ሙያ የህዝብ ጥቅምን ማስጠበቁን ማረጋገጥ፤

፭/ የሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎችን የሙያ ነፃ ነት ማስከበር።

1/"Proclamation" means the Financial Reporting Proclamation No 847/2014;

2/"Firm" means a firm which provides accounting service or audit service and registered as such by the board.

3/ "Professional" means a person who is registered by the board as a certified public accountant or a certified auditor and received certificate of registration or a practicing certificate as the case maybe;

4/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation.

## PART TWO
## ACCOUNTING AND AUDITING BOARD OF ETHIOPIA

### 3. Establishment

1/ The Accounting and Auditing Board of Ethiopia (hereinafter the "Board") is hereby established as an autonomous government organ having its own legal personality.

2/ The Board shall be accountable to the Ministry.

### 4. Head Office

The Board shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

### 5. Objectives of the Board

The Board shall have the following objectives:

1/ promote high quality reporting of financial and related information by reporting entities;

2/ promote the highest professional standards among auditors and accountants;

3/ promote the quality of accounting and auditing services;

4/ ensure that the accounting profession is used in the public interest;

5/protect the professional independence of accountants and auditors.

## ፮. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ለቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ ፬ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ዓለም አቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል ከሚያወጣው የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጣመ የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የሚመሩበት የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፣ ይፋ ያደርጋል እንዲሁም በየጊዜው ይገመግማል።

፪/ የባለሙያዎችን ማመልከቻ ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ፣ ባለሙያዎችን ስለማገድ ወይም ከባለሙያዎች ዝርዝር ስለመሠረዝ፣ ፈቃድ ስለማደስ እና ሌሎች ባለሙያዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎች ያወጣል።

፫/ የራሱን የፈተና እና የብቃት መሥፈርት መመሪያዎች ያወጣል።

፬/ የሂሣብ ሙያን እና የባለሙያዎችን አቅም ለማጎልበት ከአገር ውስጥና ውጭ ሀገር ካሉ አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣኖች፣ ማህበራት፣ የህብረተሰብ ተቋሞች ወይም አካላት ጋር ይነጋገራል፣ ይመካከራል፣ ግንኙነት ያደርጋል ወይም ይተባበራል።

፭/ ዓላማውና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ ማናቸውም አለም አቀፍ አካል ጋር ይተባበራል ወይም የዚህ አይነቱ አካል አባል ወይም ተባባሪ አባል ይሆናል።

፮/ በባለሙያዎች እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በግልግል ወይም በዕርቅ መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል።

፯/ በሂሣብ ሙያ ላይ ተጽዕኖ ባላቸው በሥራ ላይ ባሉ ወይም ረቂቅ ህጎች ላይ የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል።

፰/ የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችን ለመመዝገብ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ይሰጣል ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፱/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሂሳብ እና ኦዲት ሥራ ሙያን ይወክላል።

## 6. Powers and Duties of the Board

The Board shall, without prejudice to the powers and duties given to it by Article 4 of the Proclamation, have the following additional powers and duties to:-

1/ establish, publish and review a Code of Professional Conduct and Ethics for certified public accountants and certified auditors, which shall be consistent with that of the International Federation of Accountants or its successors;

2/ issue directives related to professionals including for the acceptance or rejection of application, suspension, cancellation or renewal of certificate and registration;

3/ issue its own examination and quality requirement directives;

4/ confer, consult, maintain contact or co-operate with any relevant authorities, associations, societies, institutions or bodies to enhance the standing of the accounting profession and professionals both nationally and internationally;

5/ cooperate with, or become a member or an affiliate of, any international body, the objectives and functions of which are similar to those of the board;

6/ facilitate arbitration or conciliation to amicably resolve disputes between professionals and their clients;

7/ consider and propose for amendment of existing or proposed legislation in Ethiopia affecting the accounting profession;

8/ conduct or arrange for the conduct of professional qualification examination for the purposes of registering certified public accountants;

9/ represent the accounting and auditing profession in Ethiopia;

፲/ እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር በመሆን በቦርዱ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የብቃት መሥፈርቶችን በማውጣት በእነዚሁ መሥፈርቶች መሠረት ባለሙያዎችን መዝግቦ ይይዛል፤

፲፩/ ለባለሙያዎች ለሚሰጡ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ፕሮግራሞች መሥፈርት ያወጣል፣ ሥልጠና ይሰጣል ወይም ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

፲፪/ በራሱ አነሳሽነት ወይም ከሌላ ሰው በሚቀርብ ጥያቄ ወይም ቅሬታ መሠረት በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ወይም በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የሚፈጸም የሥነምግባር ደንብ ወይም የዚህን ደንብ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍን አስመልክቶ የቀረበን ክስ ይመረምራል፤ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫/ የላቀ የኦዲት ሥራ ጥራት መኖሩን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት በሥራ ላይ ያውላል፤

፲፬/ ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች የሚሠሩ ኦዲተሮችን የሥራ ጥራት ይመረምራል ወይም እንዲመረመር ያደርጋል፤

፲፭/ የሂሣብና የኦዲት ሙያን የሚመለከቱ አለም አቀፍና የሀገር ውስጥ መረጃዎችን በየጊዜው በመከታተል ለባለሙያዎች እና ለሌሎች ሰዎች ያሰራጫል፤

፲፮/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

**፯. <u>የቦርዱ አቋም</u>**

፩/ ቦርዱ፦

ሀ) የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

ለ) በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

ሐ) አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

፪/ ቦርዱ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያግዙትን የተለያዩ የአማካሪ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

10/lay down the requirements to register persons who qualify to be certified public accountants or certified auditors and register such persons as professionals and maintain a list of such persons;

11/establish requirements for, conduct, or arrange for the conduct of continuing professional training programs;

12/inquire into any breach of the Code of Professional Conduct and Ethics of the Board, the provisions of this Regulation or Regulations or directives issued under the proclamation, any certified auditor or certified public accountant, either on its own initiative or at the request or grievance of any person and take disciplinary action where appropriate;

13/implement a sound quality assurance mechanisms to ensure high quality audit practice;

14/conduct or arrange for the conduct of practice review of the auditors of small and medium enterprises;

15/engage in the continuous review and dissemination of international and domestic informations to professionals and others concerning to professions of accounting and auditing;

16/perform such other related functions as are necessary for the achievement of its objectives.

**7. <u>Organization of the Board</u>**

1/ The Board shall have:

a) a Board of Directors;

b) a Director General and, as may be necessary, a Deputy Director Generals, to be appointed by the Government; and

c) the necessary staff.

2/The Board may establish various advisory committees to assist it in discharging its responsibilities properly.

**፰. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት**

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ከግሉ ዘርፍና ሙያውን ከሚወክሉ የሙያ ማህበራት የተውጣጡ ፲፪ አባላት ይኖሩታል።

፪/ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡት አብዛኞቹ ሰዎች በሂሳብ ሙያ እና ለሙያው ቀረቤታ ካላቸው የትምህርት መስኮች ይሆናሉ።

**፱. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን**

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ለሌላ ሦስት ዓመት በአባልነት በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል።

፫/ ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመናት ያገለገለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ከኃላፊነት ከተነሳ ከሦስት ዓመታት ቆይታ በኋላ በድጋሚ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ሊመረጥ ይችላል።

**፲.የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር**

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የቦርዱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤

፪/ ለመንግሥት የሚቀርበውን የቦርዱን በጀትና የሥራ ፕሮግራም እና ሪፖርት ይመረምራል፤

፫/ ቦርዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖች ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይመረምራል።

**፲፩.የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ**

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።

፪/ በማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

**8. Members of the Board of Directors**

1/ The Board of Directors shall, including the chairperson, have 12 members to be appointed by the government from the relevant government organs, higher education institutions, and the private sector and from associations representing the profession.

2/ The majority of the persons to be appointed as members of the Board of Directors shall be from accounting and other related disciplines.

**9. Term of office of Members of the Board of Directors**

1/ Term of office of members of the Board of Directors shall be three years.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, any member of the Board of Directors may be reappointed to serve in the board for another term of three years.

3/ A member of the Board of Directors appointed to serve as such in the board for two consecutive terms may be reappointed after a three years' interval.

**10. Powers and Duties of the Board of Directors**

The Board of Directors shall have the powers and duties to:

1/ oversee the activities of the Board;

2/ review the budget and work program and reports of the board prior to their submission to the government;

3/ review the rates of fees to be paid for services rendered by the board prior to their submission to the government.

**11. Meetings of the Board of Directors**

1/ The Board of Directors shall meet regularly once in a month; provided, however, that extraordinary meeting of the Board of Directors may be called by the Chairperson or when at least two third of the members request for such a meeting at any time.

2/ There shall be a quorum where two third of the members are present at any meeting.

፫/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬/ የቦርዱ ዋና ዳይሬክተር በስብሰባ ላይ እንዳይገኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካልወሰነ በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፲፪.ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ አለመሆንና ከአባልነት ስለመሰናበት**

፩/ ማንኛውም ሰው፦

ሀ) በማንኛውም ጊዜ በሙስና፣ በስርቆት፣ በማጭበርበር፣ አስመስሎ በመስራት፣ በሀሰት በመመስከር፣ ወይም በማናቸውም የእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፣

ለ) ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ሕግ መሰረት የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው ከስድስት ወር ባላነሰ የእስራት ቅጣት በሚያስቀጣ ወንጀል ተግባር የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈበት ከሆነ፣

ሐ) በአባልነት ቢሾም የጥቅም ግጭት የሚያስከትልበት ከሆነ፣

መ) በሌላ ማናቸውም ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ባለአደራ ለማገልገል በሕግ ብቁ ካልሆነ፣

ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ ሊሆን አይችልም።

፪/ ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ይሰናበታል፦

ሀ) በራሱ ፈቃድ ከአባልነት ለመሰናበት ለሚኒስትሩ የጽሑፍ ማመልከቻ ሲያቀርብ፣

ለ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ያወጣውን የአባላቱን የሙያና የሥነምግባር ደንብ ጥሶ ሲገኝ፣

3/ Decisions of the Board of Directors shall be passed by a majority vote; provided, however, that the chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

4/ The Director General of the Board shall, unless otherwise excused by the Board of Directors, attend every meeting of the Board of Directors without voting right.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board of Directors may adopt its own rules of procedure.

**12.Disqualification and Removal of Members of the Board of Directors**

1/ A person shall not qualify to be a member of the Board of Directors, if that person:

a) has at any time been convicted of an offence involving corruption, theft, fraud, forgery, perjury or other acts of dishonesty;

b) has, within the past five years been convicted of a criminal offence under any law punishable by a term of imprisonment of no less than six months without the option of a fine;

c) would have a conflict of interest if appointed as a member;

d) would for any other reason be disqualified by law from serving as a trustee in Ethiopia.

2/ A person shall be removed from membership of the Board of Directors, if that person:

a) submits a resignation request to the Minister in writing;

b) has committed a breach of the Code of Conduct and Ethics adopted by the board;

ሐ) በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አብላጫ ድምጽ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት አልተወጣም ተብሎ ሲወሰን፤ ወይም

መ) በአስራ ሁለት ተከታታይ ወራት ውስጥ ከተደረጉ ስብሰባዎች ቢያንስ በግማሹ ላይ ካልተገኘ።

## ፲፫. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የቦርዱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የቦርዱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የቦርዱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የቦርዱን ዓላማ በማስፈፀም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የቦርዱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከታዬ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለቦርዱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ቦርዱን ይወክላል፤

ረ) የቦርዱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በዳይሬክተሮች ቦርድ ከታየ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

c) unable to discharge the responsibilities as a member of the Board of Directors as shall be determined by a majority vote of the members thereof; or

d) fails to attend at least half of the meetings of the Board of Directors over a period of 12 consecutive months.

## 13. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the board and shall, subject to the general direction of the Board of Directors, direct and administer the activities of the board.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall have the powers and duties to:-

a) exercise the powers and duties of the board stated under Article 6 of this regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the board in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees engaged in the core functions of the board, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and, upon review by the Board of Directors, submit to the Ministry the work program and budget of the board, and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the board;

e) represent the board in its dealings with third parties;

f) prepare and, upon review by the Board of Directors, submit to the Ministry the performance and financial reports of the board.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለቦርዱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቦርዱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**፲፬. የበጀት ምንጭ**

የቦርዱ የበጀት ምንጮች፦

፩/ መንግሥት ከሚመድብለት ዓመታዊ በጀት፣ እና

፪/ ከሌሎች ምንጮች ይሆናል።

**፲፭.ስለሂሣብ መዛግብት**

፩/ ቦርዱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የቦርዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ክፍል ሦስት
## ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ፣ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት እና ስለመቆጣጠር

**፲፮. ስለመዛግብት**

ቦርዱ የባለሙያዎችን ስምና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች የያዘ መዝገብ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል።

**፲፯. የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ**

፩/ በሂሣብ ሙያ አግባብነት ያላቸው የብቃት መስፈርቶችን የሚያሟላና ቢያንስ የሦስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ማንኛውም ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ለመመዝገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርምና ሥርዓት መሠረት ማመልከት ይችላል።

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀፅ ፩ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያና በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰኑ መረጃዎች ጋር እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the board to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the board.

**14.Source of the Budget**

The Board's budget shall be drawn from the following sources:

1/ annual budget allocated by the government; and

2/ from other sources.

**15.Books of Accounts**

1/ The Board shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the board shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor assigned by Auditor general.

## PART THREE
## REGISTRATION, CERTIFICATION AND MONITERING OF PROFESSIONALS

**16.Registers**

The Board shall keep, maintain and update registers of professionals specifying the name and all relevant particulars of every professional, and registers of any other matter it deems necessary specifying the relevant information regarding the matter.

**17.Registration of Certified Public Accountants**

1/ any person who satisfies the requirements relating to qualifications in the field of accountancy and has a minimum of three years' practical experience in the field may apply to the board to be registered as a certified public accountant in such form or manner as may be prescribed by the board.

2/ The Board may require an application under sub-article (1) of this Article to be accompanied by the prescribed fees and such information as may be determined by the board in its directives.

፫/ ቦርዱ፦

ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለውን ወይም ኢትዮጵያዊ ካልሆነ የሥራ ፈቃድ ያለውን ወይም የሥራ ፈቃድ ከማቅረብ ግዴታ በሕግ ነፃ የተደረገን፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ የሆነን፤

ሐ) መልካም ሥነ ምግባር ያለውና እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል በማንኛውም ሀገር ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘን፤

መ) በቂ የሂሣብ ሙያ እውቀትና ክህሎት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጠውን ፈተና ወይም ምዘና ያለፈን፤ እና

ሠ) ተገቢውን ክፍያ የከፈለን፤

አመልካች ስምና አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ ይመዘግበዋል።

፬/ ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ መሥራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል።

**፲፰.<u>የተመሰከረላቸውን ኦዲተሮች ስለመመዝገብ</u>**

፩/ ኦዲተር በመሆን ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ እንደተመሰከረለት ኦዲተር እንዲመዘገብ ቦርዱ በሚያወጣው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት ለቦርዱ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስኑ መረጃዎች ጋር መቅረብ አለበት።

3/ The Board shall register the applicant as a certified public accountant and enter his name and such particulars as it considers relevant, in the register of certified public accountants where the applicant:

a) is a citizen of Ethiopia, or where he is a non-citizen, he holds a work permit or is legally exempt from holding a work permit;

b) is a permanent resident in Ethiopia;

c) is of good character and has not been convicted of an offence involving fraud or dishonesty in any country;

d) has successfully undergone such exam ination or assessment to be given for the purpose of determining whether he possesses adequate professional accountancy know ledge and skills; and

e) has paid the prescribed fees.

4/ The Board may require, as a condition for a certified public accountant to be allowed to remain in practice, that the certified public accountant comply with any continuing professional education as may be specified in the directives of the board.

**18.<u>Registration of Certified Auditors</u>**

1/ Any certified public accountant who intends to practice as an auditor may apply in writing to the board to be registered as certified auditor in such form and manner as may be prescribed by the board.

2/ An application under sub-article (1) of this Article shall be accompanied by the prescribed fees and such information as may be determined by the board in its directives

፫/ ቦርዱ አመልካቹ፦

ሀ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ መሆኑን፤

ለ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን፤

ሐ) ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት ለመውሰድ ዝግጅት ማድረጉን፤

መ) እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመስራት የሚያስችል ብቃት ያለውና ቦርዱ ባወጣው መመሪያ የሚጠየቀውን ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርት በፈጸመበት እና በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻውን ባቀረበበት ጊዜ መካከል አንድ ዓመት ያለፈ መሆኑን፤ እና

ሠ) ቦርዱ በሚወስነው ጊዜና አኳኋን መሠረት ለጥራት ማረጋገጫ ምርመራ እራሱን ያዘጋጀ መሆኑን፤

ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ስምና ሌሎች መረጃዎች በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደተመሰከረለት ኦዲተር ይመዘግበዋል።

፬/ ቦርዱ አንድ ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር መስራት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሠረት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ትምህርትና ስልጠና የመውሰድ ግዴታን እንዲያሟላ ሊጠይቀው ይችላል።

፲፱. **የተመሰከረላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች እና የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ስላለመመዝገብ**

፩/ ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ወይም ፲፰ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት፦

ሀ) እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፦

(፩) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፤

(፪) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፤ ወይም

3/ The Board may register an applicant as a certified auditor and enter his name and such particulars as it considers relevant in the register of certified auditors, where it is satisfied that the applicant:

a) is a certified public accountant;

b) meets the requirements laid down in the directives of the board;

c) has made such arrangements as may be provided in the directives of the board, for continuing professional education;

d) has the necessary competence to practice as a certified auditor and a period of one year has elapsed between the date he has undertaken continuing professional education as provided by the directives of the board and the date of the application; and

e) subjects himself to quality assurance reviews at such time and in such manner as the board may prescribe.

4/ The Board may require, as a condition for a certified auditor to be allowed to remain in practice that he has to comply with any continuing professional education and training as may be specified in the directives of the board.

19. **Refusal to Register Certified Public Accountants and Certified Auditors**

1/ On receipt of an application under Article 17 or 18 of this regulation, the board shall:

a) refuse to register an applicant as a certified public accountant where the applicant:

(1) does not satisfy the requirements specified in sub-article (3) of Article 17 of this regulation;

(2) has had his license or approval to practice as a certified public accountant suspended, cancelled or withdrawn in any country; or

(፫) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተ መሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመ ዝገብ ብቁ ካልሆነ፤

አመልካቹን እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ አይመዘግበውም።

ለ) እንደተመሰከረለት አዲተር ለመመዝገብ የቀረበው አመልካች፦

(፩) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱትን መሥፈርቶች ካላሟላ፤

(፪) የተመሰከረለት አዲተር ሆኖ እንዲሠራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፤ ወይም

(፫) በሌላ ማንኛውም ምክንያት እንደተ መሰከረለት አዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፤

አመልካቹን እንደተመ ሰከረለት አዲተር አይመዘግበውም።

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበን ሰው ላለመመዝገብ ሲወስን ምክንያቱን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

፫/ ቦርዱ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት አዲተር ስላልመዘገበው ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ሊያስቀይር በሚችል የሕግና የፍሬ ነገር ትንታኔ በማስደገፍ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ቅሬታውን በጽሑፍ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሊያቀርብ ይችላል።

፬/ የዳይሬክተሮች ቦርድ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

## ፳. ድርጅቶችን ስለመመዝገብ

፩/ ማንኛውም የሂሳብ ሙያ አገልግሎት ወይም የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ድርጅት ቦርዱ እንዲመዘግበው ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ሥርዓት መሠረት በጽሑፍ መቅረብ አለበት።

(3) is otherwise unfit to be registered as a certified public accountant;

b) refuse to register an applicant as a certified auditor where the applicant:

(1) does not satisfy the requirements specified in sub-article (3) of Article 18 of this regulation;

(2) has had his license or approval to practice as a certified auditor susp ended, cancelled or withdrawn in any country; or

(3) is otherwise unfit to be registered as a certified auditor.

2/ Where the Board decided to refuses to register an applicant under this Article, it shall inform the applicant in writing of its refusal within five working days.

3/ A person aggrieved by the refusal of the board to register him as a certified public accountant or certified auditor, may within 30 days of receipt of the decision of the board apply in writing to the Board of Directors for review of the decision of the board and such application shall set forth any facts or legal analysis that would support a decision to register him.

4/ The decision of the Board of Directors shall be the final decision of the board.

## 20.Registration of Firms

1/ Any firm that intends to provide accounting services or audit service may apply to the board for registration.

2/ An application under sub-article (1) of this Article shall be made in writing in such form and manner as may be prescribed by the board.

፫/ ቦርዱ፦

ሀ) ሁሉም የድርጅቱ ሸሪኮች በቦርዱ የተመዘገቡ መሆኑን፤

ለ) ድርጅቱ እና እያንዳንዱ ሸሪክ አባል በተናጠል ቦርዱ የሚያወጣውን የሙያ ስነምግባር ደንብ ለማክበር በጽሑፍ ግዴታ የገቡ መሆኑን፤

ሐ) ድርጅቱ ቦርዱ በሚወስነው የገንዘብ መጠን የሙያ መድን የገባ ወይም ሌላ ዓይነት የገንዘብ ዋስትና የሚያቀርብ መሆኑን፤

ሲያረጋግጥ የአመልካቹን ድርጅት ስም እና ሌሎች መረጃዎች በድርጅቶች መዝገብ ላይ በማስፈር እንደ ድርጅት ይመዘግበዋል።

፬/ የድርጅት ምዝገባን በሚመለከት ለሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ፳፩. የምዝገባ እና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት

፩/ ቦርዱ አንድን ግለሰብ እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም አንድን ድርጅት እንደ ድርጅት ሲመዘግብ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

፪/ ቦርዱ አንድን ሰው እንደተመሰከረለት ኦዲተር ሲመዘግበው የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

፫/ የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት አመልካቹ ተገቢውን ክፍያ ሲፈጽም ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም መሠረት ይሰጣል።

፬/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት፦

ሀ) እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ብሎ መጥራት እና "ሲ.ፒ.ኤ." የሚለውን ምህጻረ ቃል መጠቀም ይችላል፤

ለ) እንደተመሰከረለት ኦዲተር የተመዘገበ ሰው ራሱን የተመሰከረለት ኦዲተር ብሎ መጥራት እና "ሲ.ኤዩ." የሚለውን ምህጻረ ቃል መጠቀም ይችላል።

3/ The Board shall register the applicant firm and enter its name and such particulars as it considers relevant in the register of Firms, upon being satisfied that:

a) all of the partners of the firm are registered with the board;

b) there is a written undertaking by the firm and the partners individually that they shall be bound by the Code of Professional Conduct of the Board ;

c) the firm holds a professional indemnity insurance of such amount or provides such other financial guarantee as the board may determine.

4/ The provisions of sub articles 2, 3 and 4 of Article 19 of this Regulation shall apply to any complaint that may be lodged in connection with the registration of firm.

## 21. Registration and Practicing Certificate

1/ Where the board registers a person as a certified public accountant or a firm as a firm, it shall issue to the person or the firm a certificate of registration.

2/ Where the board registers a person as a certified auditor, it shall issue to him a practicing certificate.

3/ A registration or a practicing certificate shall, upon payment of the prescribed fees by the applicant, be issued in such form as may be prescribed by the board.

4/ A person who is registered under the provisions of this part as:

a) a certified public accountant shall be entitled to describe himself as certified public accountant and to use the initials "C.P.A.";

b) a certified auditor shall be entitled to describe himself as certified auditor and to use the initials "C.Au.".

፭/ የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆየው የምስክር ወረቀቱን የያዘው ሰው ምዝገባ እስከፀና ድረስ ብቻ ይሆናል። ምዝገባው የተሰረዘ ወይም የታገደ ማንኛውም ሰው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ለቦርዱ ወዲያውኑ መመለስ አለበት።

## ፳፪. ምዝገባን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

፩/ ቦርዱ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ምዝገባ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ እና ከመዝገብ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፦

ሀ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ የተመዘገበው በማጭበርበር ወይም በማስመሰል መሆኑን ሲደርስበት፤

ለ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ማንኛውንም የቦርዱን መመሪያ የማያከብር ሲሆን ወይም የሚጥስ ተግባር መፈፀሙ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ አባል ከሆነበት ሌላ የሂሳብ ሙያ ማህበር የታገደ ወይም የተሰረዘ ሲሆን፤

መ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ አዋጁን ወይም ይህንን ደንብ ተላልፎ ከተገኘ፤

ሠ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ ከእምነት ማጉደል ጋር በተያያዘ ወንጀል በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ጥፋተኛ ሆኖ የገንዘብ ቅጣት አማራጭ በሌለው እስር ከተቀጣ ወይም ድርጅቱ የገንዘብ ቅጣት ከተጣለበት፤

ረ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው ወይም የተመሰከረለት ኦዲተሩ በሕግ ችሎታ ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሰ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያው፣ የተመሰከረለት ኦዲተሩ ወይም ድርጅቱ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠቱ ሲረጋገጥ።



5/ A certificate of registration or a practicing certificate shall remain valid for so long as its holder remains registered. A person whose registration is cancelled or suspended shall immediately return his certificate of registration or practicing certificate to the board.

## 22. Cancellation or Suspension of Registration

1/ The Board may either suspend or cancel the registration of a certified public accountant, a certified auditor or a firm, and remove from the register where:

a) the certified public accountant or the certified auditor or the firm has obtained registration by fraud or mis representation;

b) the certified public accountant or the certified auditor or the firm no longer satisfies or has acted in breach of any directive of the board;

c) the registration of the certified public accountant or certified auditor has been suspended or cancelled by other professional accountancy body of which he is a member;

d) the certified public accountant or the certified auditor or the firm has acted in breach of the provisions of the Proclamation and this regulation;

e) the certified public accountant or the certified auditor has been convicted of an offence involving dishonesty, whether in Ethiopia or abroad jurisdiction for which he could have been sentenced to imprisonment without the option of a fine or in case of the firm with fine;

f) the certified public accountant or the certified auditor becomes legally interdicted.

g) the certified public accountant or the certified auditor or the firm has submitted incorrect information to the Tax Authority.

፪/ ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲሰርዝ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያዎች መዝገብ ይሠርዘዋል።

፫/ ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ የምስክር ወረቀቱ ለታገደበት ጊዜ የምስክር ወረቀቱን የያዘውንም ሰው ከባለሙያነት ያግደዋል።

፬/ ቦርዱ የምዝገባን ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀትን ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ይህንኑ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሦስት ተከታታይ ቀናት በማውጣት ህዝብ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት።

**፳፫. <u>የምዝገባ የቆይታ ጊዜ እና እድሳት</u>**

፩/ ቦርዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የሚሰጠው የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል።

፪/ ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል።

፫/ ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት ቦርዱ በሚያዘጋጀው ፎርም እና ስርዓት መሠረት የጽሑፍ ማመልከቻ በማስገባት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ማሳደስ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው ክፍያ እና ቦርዱ በመመሪያ ከሚወስነው መረጃ ጋር መቅረብ አለበት።

፭/ ቦርዱ፦

ሀ) አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለ ሙያ ወይም ድርጅት እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፤

2/ Where the board cancels a registration or practicing certificate, it shall also cancel the holder of the certificate from the professionals' registration list of the board.

3/ Where the board suspends a registration or practicing certificate, it shall suspend the holder of the certificate from any professional services for the period for which the certificate has been suspended.

4/ Where the board suspend or cancel a registration or practicing certificate shall publish a notice, for three consecutive days, in not less than two daily newspapers of national circulation notifying the public of such cancellation or suspension.

**23.<u>Duration and Renewal of Registration</u>**

1/ A registration or practicing certificate issued in accordance with sub-article (1) or (2) of Article 21 of this regulation shall be valid for a period to be determined by the board.

2/ Any certified auditor may renew his practicing certificate by filing a written application to the board, not later than one month before the expiry of the practicing certificate, in such form and manner as the board may prescribe.

3/ Any certified public accountant or firm may renew the certificate of registration by filing a written application to the board, not later than one month before the expiry of the certificate of registration, in such form and manner as the board may prescribe.

4/ An application under sub-article (2) or (3) of this Article shall be accompanied by the prescribed fees and such information as the board may determine in its directives.

5/ The Board shall:

a) renew the certificate of the certified public accountant or the firm if the applicant satisfies the requirements specified in sub-article (3) of Article 17 or sub-article (3) of Article 20 of this regulation, respectively;

ለ) አመልካቹ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለ ሙያ ወይም ድርጅት፦

(፩) እንደአግባብነቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፤ ወይም

(፪) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተ መሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም ድርጅት ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ፤

የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን አያድስ ለትም።

ሐ) አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያ ሟላ ከሆነ የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱን ያድስለታል፤

መ) አመልካቹ የተመሰከረለት ኦዲተር፦

(፩) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫)እና(፬) የተመለከቱትን መሥፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፤ ወይም

(፪) የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ እንዲ ሰራ የተሰጠው ፈቃድ በየትኛውም ሀገር ከታገደ፣ ከተሠረዘ ወይም ከተወሰደ፤ ወይም

(፫) በሌላ ማናቸውም ምክንያት እንደተ መሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ ብቁ ካልሆነ ፤

የሙያሥራ የምስክር ወረቀቱን አያድስ ለትም።

፮/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የአንድን አመልካች የምስክር ወረቀት ላለማደስ ሲወስን የምስክር ወረቀቱን የማያድስበትን ምክንያት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

## ፳፬. ያለምስክር ወረቀት መሥራትን ስለ መከልከል

ማንኛውም ሰው ቦርዱ የሚሰጠው ሕጋዊ የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ወይም የምስክር ወረቀቱ በሚፈቅደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ሆነ

b) refuse to renew the certificate of the certified public accountant or the firm where the applicant:

(1) does not satisfy the requirements specified in sub-article (3) of Article 17 or sub-article (3) of Article 20 of this regulation, respectively; or

(2) is otherwise unfit to be registered as a certified public accountant or a firm.

c) renew the certificate of the certified auditor if the applicant satisfies the requirements specified in sub-articles (3) and (4) of Article 18 of this regulation;

d) refuse to renew the certificate of the certified auditor where the applicant:

(1) does not satisfy the requirements specified in sub-articles (3) and (4) of Article 18 of this regulation; or

(2) has had his license or approval to practice as a certified auditor suspended, cancelled or withdrawn, in any country; or

(3) is otherwise unfit to be registered as a certified auditor.

6/ Where the Board decided to refuses renewal of a certificate under this Article, it shall inform the applicant in writing of its refusal within five working days.

## 24. Prohibition against Practicing without Certificate

No person shall practice or hold him-self out as a certified public accountant or certified auditor whether directly or indirectly, by himself or in partnership or association with any other person, except in accordance with the terms and conditions

በተዘዋዋሪ በእራሱም ሆነ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር በሽርክና ወይም በማኅበር እንደተመሰከረ ለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንደተመሰከረለት ኦዲተር መሥራት ወይም እራሱን ማቅረብ አይችልም።

of a valid certificate of registration or practicing certificate issued by the board

**፳፭. <u>የስም ወይም የሌላ መረጃ ለውጥ</u>**

ማንኛውም የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት በተመዘገበው ስሙ ወይም ሌላ መረጃ ላይ ለውጥ ሲኖር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለውጡ በተደረገ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

**25. <u>Change of Name or Particulars</u>**

Any certified public accountant, certified auditor or firm shall, whenever there is a change in the registered name or particulars, notify the board of such change within 14 days of the change occurring in such manner as the board may require in its directives.

**፳፮. <u>የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ስለ ማከናወን</u>**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ የሚፈቅድለት የሌላ ሀገር የሂሣብ ሙያ ተቆጣጣሪ ድርጅት፣ አህጉራዊ ወይም ክፍለ አህጉራዊ የሂሣብ ሙያ ማህበር ወይም ሌላ አለም አቀፍ የሂሣብ ሙያ ማህበር የተመሰከረላቸው ኦዲተሮችን ሥራ ጥራት መመርመር ይችላል። ለዚህ ዓላማ፦

ሀ) በኦዲተሩ፣ በሸሪኩ፣ በተቀጣሪው ወይም ከእርሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሰው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለውን መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀትና ማህደር፣ ሰነድና መዝገብ መመርመርና ፎቶ ኮፒ መውሰድ፣ ወይም አጭር ማስታወሻ መያዝ ይችላል፤

ለ) ከኦዲተሩ፣ ከሸሪኩ ወይም ከተቀጣሪው ወይም ከኦዲተሩ ጋር የሥራ ግንኙነት ካለው ሰው ማንኛውንም መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ማንኛውም የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ሸሪኩ፣ ተቀጣሪው ወይም ከሱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው በቦርዱ ወይም ቦርዱ በጽሑፍ በወከለው ሰው ሲጠየቅ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለን ማንኛውንም አግባብነት ያለው መዝገብ፣ የኦዲት ሥራ ወረቀት፣ ማህደር ወይም ሰነድ ማቅረብ አለበት።

**26.<u>Quality Assurance Review of Certified Auditors</u>**

1/ Without prejudice to the provision of Article 25 of the Proclamation, the board, or any other countries' accountancy regulatory agencies, regional and sub-regional accountancy association and other international accountancy association, authorized by the board in writing, may review the practice of certified auditors and for that purpose, are authorized to:

a) inspect any relevant book, audit working papers and files, document and record in the possession, or under the control of the auditor, his partner, employee or persons associated with the auditor and make copies of or take any abstract of or extract from any such book, document and record; and

b) seek information or clarification from any partner, employee or persons associated with the auditor.

2/ For the purposes of sub-article (1) of this Article any certified auditor, his partner, employee or person associated with the auditor shall, at the request of the board or any person authorized by it in writing, produce any relevant book, audit working papers and files, document or record in his possession or under his control.

**፳፯. መረጃን ይፋ ስለማድረግ**

፩/ ቦርዱ፦

ሀ) የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሁለት በማያንሱ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ዕለታዊ ጋዜጣዎች ለሦስት ተከታታይ ቀናት ዓመታዊ የባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በማውጣት ይፋ ማድረግ አለበት፤

ለ) ለህዝብ ይፋ በሆነ መዝገቡ እና በድረ-ገጹ ወቅታዊውን የባለሙያዎች ስም ዝርዝር መያዝ አለበት።

፪/ የባለሙያዎችን መዝገብ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ ማየት ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው አመቺ በሆነ ማንኛውም ጊዜ ክፍት ይሆናል።

፫/ ቦርዱ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች የያዘ ሪፖርት በየጊዜው ያወጣል።

፬/ ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን መረጃ የያዘ ኤሌክትሮኒክ መጽሔት የሚያወጣበት ድረ-ገጽ ይኖረዋል።

፭/ቦርዱ ከባለሙያዎች እና ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች በሪፖርቱ ወይም በድረ-ገጹ፣ በኤሌክትሮኒክ መጽሔቱ ወይም በዕለታዊ ጋዜጣ ይፋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

## ክፍል አራት
## ትምህርት እና ፈተናዎች

**፳፰. የሙያ ብቃት መስፈርቶች እና የትምህርት ፕሮግራም ይዘቶች**

ቦርዱ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የመንግስት እና የግል ዘርፍ ፍላጎቶችን ማሟላት በሚያስችል አኳኋን የሙያ ብቃት መስፈርቶችን እና የትምህርት ፕሮግራም ይዘቶችን ያዘጋጃል።

**፳፱. የፈተና አስተዳደር እና የጥራት ማረጋገጫ**

የቦርዱ የሙያ ብቃት መስፈርቶች ከፍተኛ ጥራትና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥና ከልምድ ልውውጥ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል ቦርዱ በፈተና አቅድ ረገድ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እሱን የሚተካ

**27. Publication**

1/The Board shall publish:

a) not later than three months after the end of its financial year, for three consecutive days, in not less than two daily newspapers of national circulation an annual list of professionals registered by the board;

b) maintain in its public register and on its website, a current list of names of professionals.

2/ The registers of professionals shall at all reasonable times be available for inspection by any person, on payment of the prescribed fee.

3/ The Board shall periodically publish an official report that shall contain such information that the Board may deem necessary.

4/ The Board may maintain an electronic homepage and publish an e-bulletin that shall contain such information that the board may deem necessary.

5/ The Board may cause to be published in its official report, on its homepage, e-bulletin or in a daily newspaper, the decisions of the board with respect to professionals and other activities of the board.

## PART FOUR
## EDUCATION AND EXAMINATIONS

**28. Professional Qualifications and Contents of Education Programs**

The Board shall, based on the standards of the International Federation of Accountants or its successors, develop qualification requirements and contents of education programs that meet the needs of both the government and private sectors efficiently and effectively.

**29 Exam Administration and Quality Assurance**

The Board shall establish twining arrangements with accountancy bodies accredited by the International Federation of Accountants or its successors and work in partnership with them in joint examination schemes for experience sharing and for ensuring that the board's qualification

አካል እውቅና ካላቸው የሂሳብ ሙያ ማህበራት ጋር ጥምረትን በመፍጠር በትብብር ይሰራል።

## ክፍል አምስት

## የዲሲፕሊን ክስ

### ፴. በቦርዱ ስለሚታይ የዲሲፕሊን ክስ

፩/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፴፮ እስከ ፵፪ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቦርዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከመርማሪ ሹሙ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሣብ ወይም ቦርዱ በራሱ ተነሳሽነት ባገኘው መረጃ መነሻ አዋጁ ወይም ይህ ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ወይም የሙያ ስነምግባር ደንብ በተመሠከረለት የሂሳብ ባለሙያ፤በተመሠከረለት ኦዲተር ወይም በድርጅት ተጥሷል ብሎ እንዲያምን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ጥሰት በፈጸመው ሰው ላይ ክስ በመመሥረት ጉዳዩን በአዋጁ አንቀጽ ፴፰ (፫) መሠረት ለሚሰየሙ የክስ ሰሚዎች ይመራል።

፪/ የክስ ሰሚዎች የቀረበውን ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተረጋግጧል ብለው ካመኑ፤ በተከሳሹ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የቅጣት ውሳኔ ያስተላልፋሉ፦

ሀ) ተከሳሹ ተግሳጽ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፤

ለ) የተከሳሹ የሙያ ሥራ ወይም የምዝገባ ምሥክር ወረቀት እንዲወሰድ፤

ሐ) ተከሳሹ ለተወሰነ ጊዜ ከሙያው እንዲ ታገድ፤

መ) የተከሳሹ ስም ከመዝገብ ላይ እንዲሠ ረዝ፤

ሠ) ተከሳሹ ከብር ፳፭ሺ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሙያ ሥራ ወረቀቱ የታገደ ወይም ስሙ ከመዝገቡ የተሠረዘ ግለሰብ ወይም ድርጅት እራሱን እንደተመሰከረለት የሂሣብ ባለሙያ፤ የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም ድርጅት ማቅረብ አይችልም፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱም እገዳው ለሚፀናበት ጊዜ

requirements are high quality and can command international recognition.

## PART FIVE

## DISCIPLINARY PROCEEDINGS

### 30. Disciplinary Proceedings of the Board

1/ Without prejudice to the provisions of Articles 36 to 42 of the Proclamation, the Chief Executive Officer, upon the recommendation of the investigative officer or based on the information the board obtains on its own initiative, is satisfied that contraventions of the proclamation or this regulation or directives or the code of conduct issued hereunder may have been committed by a certified public accountant, certified auditor or firm, he may institute proceedings against the alleged violator and refer the case to the Hearing Examiners to be established pursuant to Sub-Article 3 of Article 38 of the proclamation.

2/ After the hearing, if,Hearing Examiners are of the opinion that the case under consideration has been proved wholly or in part, it shall make a finding to that effect and may make any one or more of the following orders against the defendant having regard to the nature and seriousness of the violation:

a) that the defendant be reprimanded or cautioned;

b) that the defendant's practicing certificate or certificate of registration be withdrawn;

c) that the defendant be suspended from practicing the profession for a specified period;

d) that the name of the defendant be removed from the register;

e) that the defendant pay a fine not exceeding Birr 25,000.

3/ No individual or firm whose practicing certificate or registration has been suspended or whose name has been removed from the register under sub-article (2) of this Article shall hold himself out as a certified public accountant, certified auditor or firm and his certificate shall be deemed to be cancelled until

ወይም በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ስሙ ተመልሶ መዝገብ ላይ እስኪሰፍር ድረስ እንደተሠረዘ ይቆጠራል።

፬/ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም፣ የክስ ሰሚዎች የይግባኙ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ውሳኔው እንዳይፈጸም ካልወሰኑ በስተቀር ተከሳሹ እንዲታገድ ወይም ስሙ ከመዝገብ እንዲሠረዝ እና የምዝገባ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀቱ እንዲወሰድ ወይም እንዲታገድ የክስ ሰሚዎች የሰጡት ውሣኔ ወዲያውኑ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ በዚህ ደንብ የተደነገገው ቢኖርም፣ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት፦

ሀ) ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ ሥራም ሆነ የኦዲት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ይህ ደንብ ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ወይም የተመሰከረለት ኦዲተር ሆኖ ለመሥራት የሚፈለገውን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል፤

ለ) በራሱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና በድርጅት ስም ለማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሣብ ወይም የኦዲት ሥራ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሰው ደንቡ ከፀናበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ድርጅቱ እንዲመዘገብለት ማመልከቻ ካቀረበ በዚህ ደንብ መሠረት ድርጅቱ ለመመዝገብ ማሟላት የሚፈለግበትን መስፈርት ባያሟላም ማመልከቻውን ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚቆጠር ከአምስት ዓመታት ያልበለጠ ጊዜ ሳይመዘገብ አገልግሎቱን መስጠት ሊቀጥል ይችላል።

the period of suspension has expired or until his name has been restored to the register following application in writing to the board.

4/ The decision of the Hearing Examiners to suspend or remove the name of any individual or firm from the register and to withdraw or suspend his certificate of registration or practicing certificate shall be effective immediately, notwithstanding any appeal which may be pending unless the hearing examiners expressly suspended the operation of their decision pending the outcome of such appeal.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 31. Transitory Provisions

1/ Notwithstanding the provisions of this regulation, any person who, immediately before the coming into force of this regulation:

a) was providing accounting or auditing services to reporting entity, may continue to provide such services for a period not exceeding five years beginning from the closing date for submitting of application for registration, if he applies for registration within six months of the entry into force of this regulation notwithstanding that he does not meet the requirements to act as a certified public accountant or certified auditor set forth in this regulation;

b) was providing accounting or audit services to a reporting entity, whether on his own account or in partnership with other persons under a firm name, may continue to provide such services for a period not exceeding five years beginning from the closing date for submitting of application for registration, if he applies for registration of the firm within six months of the entry into force of this regulation notwithstanding that he does not meet the requirements to operate under a firm name set forth in this regulation.

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሳይመዘገብ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ወይም ድርጅት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ እና ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ቦርዱ የሚያወጣውን መሥፈርት ካላሟላ ከአምስት ዓመት በኋላ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

**፴፪. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቦርዱ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፴፫. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን በድጋሚ ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፪/ ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

**፴፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ The application of a person or a firm allowed under this Article to continue providing accounting or audit services without registering in accordance with this regulation shall be rejected after five years, if such person or firm fails to meet the requirements for registration set forth in this regulation within five years from the closing date for submitting of application for registration.

**32. Power to Issue Directives**

The Board may issue directives necessary for the proper implementation of this regulation.

**33. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ Sub-article (3) of Article 5 of the Ethiopian Civil Service College Re-establishment Council of Ministers Regulation No.121/2006 is hereby repealed.

2/ No regulation or directive shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this regulation, be applicable with respect to matters provided for by this regulation.

**34. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of January, 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**